የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ ጥር ፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 10
ADDIS ABABA, 12th January 2017

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፱፻፺/፪ሺ፱ ዓ.ም

ለአዲስ አበባ ከተማ ፈጣን የአውቶቡስ መስመር ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ......................................................ገፅ ፱ሺ፭፻፭

## CONTENT

Proclamation No. 990/2017

Agence Fransiase De Development (AFD) Credit Facility Agreement for additional Financing of the Addis Ababa City Bus Rapid Road Transit Project Ratification Proclamation..........................................................page 9505

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፺/፪ሺ፱

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል የተደረገውን የተጨማሪ ብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለአዲስ አበባ ከተማ ፈጣን የአውቶቡስ መስመር ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፴፭ ሚሊዮን ዩሮ (ሰላሳ አምስት ሚሊዮን ዩሮ) የሚያስገኘው የተጨማሪ ብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል ሀምሌ ፳፩ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህ የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሳስ ፲፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## PROCLAMATION No.990 /2017

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT FACILITY AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AGENCY FRANCEISE DE DEVELOPMENT(AFD)

**WHERE AS**, a Credit Facility Agreements between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Agence Franciase De Development (AFD) provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit Facility in an amount of 35,000,000,00 (thirty five million)EURO for additional Financing of the Addis Ababa City Bus Rapid Transit Project was signed in Addis Ababa on the 28th day of July 2016;

**WHERE AS,** the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Credit Facility Agreement at its session held on the 27th day of December 2016,

**NOW THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed



www.chilot.me

ሕገመንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል:-

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለአዲስ አበባ ከተማ ፈጣን የአውቶቡስ መስመር ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፺/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪.የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል ሀምሌ ፳፩ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የተጨማሪ ብድር ስምምነት ቁጥር 1046 03 R በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስልጣን**

የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፴፭ ሚሊዮን ዩሮ (ሰላሳ አምስት ሚሊዮን ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the " Agence Fransiase De Development (AFD) Credit Facility Agreement for additional Financing of the Addis Ababa City Bus Rapid Transit Project Ratification Proclamation No.990/2017"

2. **Ratification of the Agreement**

The Credit Facility Agreement Number 1046 03 R signed in Addis Ababa on the 28th day of July ,2016 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Agence Franciase De Development (AFD) is hereby ratified.

3. **Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilisation of the Credit Facility amount of 35,000,000,00 (thirty five million) EURO in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Facility Agreement.

4. **Effective Date**

Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 12th day of January 2017**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me